# ምርጫ ውጤታማ ሆኖ በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተከናውኗል፡፡

***በዛሬው ምርጫ 32 የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመሳተፍ ተመዝግበው 31 የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው እየተወዳደሩ ይገኛሉ፡፡***

በዛሬው እለት ከጠዋቱ 12፡00 ሰአት ጀምሮ በአዲስ አበባ እና በክልሎች የተካሄደው የአካባቢና የማሟያ ምርጫ ከዚህ ቀደም ከነበሩት ምርጫዎች ውጤታማ ሆኖ በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ተከናውኗል፡፡

ይህ ምርጫ ከቀድሞ ምርጫዎች የበለጠ ቁጥር ያለው ከ26 ሚሊዮን ህዝብ በላይ በመራጭነት ተመዝግቧል፡፡ ከዚህ ቀደም ከነበሩት እጩዎች የበለጠ ቁጥር ያለው ከ4 ሚሊዮን በላይ እጩ ተወዳዳሪዎች የሚፎካከሩበት ምርጫ ነው፡፡ በዛሬው ምርጫ 32 የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመሳተፍ ተመዝግበው 31 የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫው እየተወዳደሩ ይገኛሉ፡፡ በዛሬው ምርጫ ከተመዘገበው መራጭ ህዝብ አብዛኛው የመረጠበት ውጤታማ ምርጫ ነበር፡፡ ከዚህ ቀደም አንድ የምርጫ ጣቢያ ለ10 ሺህ ህዝብ የሚያገለግል የነበረ ሲሆን በዛሬው ምርጫ ግን አንድ ምርጫ ጣቢያ ለ1 ሺህ ህዝብ ብቻ እንዲያገለግል ሆኖ ተደራጅቷል፡፡ ይህም በምርጫ ጣቢያዎች ሊኖር የሚችለውን ከፍተኛ መጨናነቅ የሚቀርፍና ለመራጩ ህዝብ ምቹ ሆኔታን ለማመቻቸት የአደረጃጀት ለውጥ የተደረገበት ምርጫ ነው፡፡ ምርጫው በህዝቡ ላይ ምንም አይነት መጉላላት ሳይደርስ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ተካሂዷል፡፡

የዛሬው የአካባቢና የሟሟያ ምርጫ በአዲስ አበባ እና በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች ከጠዋቱ 12፡00 ሰአት ጀምሮ ያለ ፀጥታ ችግር በሰላም ተከናውኗል፡፡ ምርጫው የህዝብ ሉዐላዊነትን ባረጋገጠና በዴሞክራሲያዊ ሁኔታ በተያዘለት እቅድ መሰረት ተጠናቋል፡፡

ሚያዝያ 5 ቀን 2000 ዓ.ም በሚካሄደው የአካባቢና የማሟያ ምርጫ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት (ኢዴኃህ) ሚያዝያ 2 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው መግለጫ ከምርጫው መውጣቱ ይታወቃል፡፡ ለምርጫው ሁለት ቀናት ሲቀሩ ከምርጫው ለመውጣት ምክንያት ሆነኝ ያለው የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች እጩዎቼን ስላሳደዱ፣ የዕጩዎች ምዝገባ ጊዜም እንዲራዘም ጠይቄ ባለመራዘሙ ነው በማለት ገልጿል፡፡ በተቃራኒው ግን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት ከምርጫው የወጣበት ምክንያት ያቀረባቸው እጩዎች ከእጩነት በራሳቸው ፈቃድ ስለወጡ፣ ከዚህም በመነሳት እንዲሁም የህዝቡን ድጋፍና ተቀባይነት ባለማግኘቱ በምርጫው እንደሚሸነፍ ሰላወቀ መሆኑ ግልፅ ነበር፡፡ ይህ የሚያመለክተውም ፓርቲው ለስልጣን ብቻ እንደሚጨነቅና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ግዴለሽ መሆኑን ነው፡፡

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሀይሎች ህብረት (ኢዴኃህ) ከምርጫው ለመውጣት ሲያስብና ከምርጫው ከወጣም በኋላ ከእርሱም ጋር አብሮት ከምርጫው እንዲወጣ የኦሮሞ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን) ላይ ግፊት ቢያደርግም፣ ኦፌዴን ግን በምርጫው መውጣት ከነበረብን ከመጀመሪያው ጀምሮ እንደነበር በአሁኑ ወቅት ከምርጫው መውጣት ከጥቅሙ ጉዳቱ እንደሚያመዝን በማመኑ በምርጫው መሳተፉን ቀጥሏል፡፡

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት ለምርጫው ሲዘጋጅ ቆይቶ ለምርጫው ጥቂት ቀናት ብቻ ሲቀሩት ወደ ኋላ በመሄድ የእጩዎች ምዝገባ ጊዜ ካልተራዘመ በምርጫው አልሳተፍም ማለቱ ፓርቲው በምርጫው እንደሚሸነፍ በመገንዘቡና ስልጣን ለመያዝ ብቻ ባለው ፍላጎት ምክንያት ከምርጫው መውጣቱን አብዛኛው ህዝብ የተረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ለምርጫ የተመዘገበው አብዛኛው ህዝብም በምርጫው በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ ተሳትፎውን ቀጥሏል፡፡